# ዐቢይ ጾም እና ንባብ

## ነገረ-መለኮታዊ እና ሳይንሳዊ እሳቦች

ፍሬሰንበት ገብረዮሐንስ

ለመንፈሳዊ መጻሕፍት ንባብ ቤተሰብ የተዘጋጀ

# 1.

# የዐቢይ ጾም በቤተክርስቲያን

# የዐቢይ ጾም በቤተክርስቲያን

- ዐቢይ ጾም በቤተ-ክርስቲያናችን እጅግ ትልቅ ቦታ ከሚሰጣቸው አጽዋማት ውስጥ ዋነኛው ነው፡፡

- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ለአርባ ቀን የጾመው ጾም ሲሆን፤ በዚህም ሰይጣንን ድል አድርጎ - መንገዱንም አብነት በመሆን እኛም እንዴት ድል እንደምናደርገው አሳይቶናል፡፡

- ይህ ጾም ‹ዐቢይ ጾም› ከመባሉ ባሻገር፤ ሁዳዴ ጾም፣ ጾመ አርባ፣ በአተ ጾም በመባል ይታወቃል፡፡

# የዐቢይ ጾም በቤተክርስቲያን

- የታሪክ መዛግብቶች እንደሚያሳዩት የጾሙ ቀደምት ታሪካዊ መሠረት ወደ መጀመሪያው መቶ ክፍለዘመን ይወስደናል፡፡

- በሁለተኛው መቶ ክፍለዘመን ቅዱስ ሄሬኔዎስ፤ ለጳጳሱ ቅዱስ ፊቅጦር (ቪክቶር) በጻፈው ደብዳቤ ላይ፤ ከፋሲካ በፊት በሚጾመው ጾም የቀናት ልክ ዙሪያ ውዝግቦች እንደነበሩ አንስቶለታል፡፡

- በዚህም ደብዳቤ ውስጥ ‹እነዚህ ውዝግቦች በእኛ ጊዜ የተከሰቱ ሳይሆን፤ ከአባቶቻችን ጊዜ ጀምሮ ቀድመው የነበሩ ናቸው› በማለት ጽፎለታል፡፡

# የዐቢይ ጾም በቤተክርስቲያን

- ጥንታዊ መሠረት ቢኖረውም፤ ጾሙ በተደራጅ መልኩ ሆኖ በአዋጅ መልክ እንዲጾም የሆነው ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ ነው፡፡

- የኒቂያ ጉባኤ ቀደምት ሰነዶች እንደሚጠቁሙት ጾሙ በተለይም ለአዳዲስ ክርስቲያኖች በትንሣኤ እለት ጥምቀትን ከመፈጸማቸው በፊት አስቀድመው በጸሎት እና በንስሃ ራሳቸውን እየመረመሩ የሚዘጋጁበት ጊዜ ነበር፡፡

- የዐቢይ ጾም ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ጥንታዊ መሠረት ያላቸው ክርስቲያኖች ሁሉም በጸሎት እና በምጽዋት ታግዘው የሚጾሙት ታላቅ እና ተናፋቂ ጾም ነው፡፡

“

**በሌላው ጊዜ የምንጾመው ጾም በፈቃዳችን ላይ የተመሠረተ ቢሆንም፤ ዐቢይ ጾምን ካልጾምን ግን ኀጢአት ይሆንብናል።**

አውግስጢኖስ

# 2.

# ቤተ-ክርስቲያን እና ንባብ

# ቤተ–ክርስቲያን እና ንባብ

- ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን የሰው ልጅ የጥበብ ሁሉ ምንጭ በሆነው አምላክ የተፈጠረ መሆኑን ታስተምራለች፡፡

- በዚህም የተነሳ የሰው ልጅ ጥበብን ማወቅ እንደሚፈልግ፤ ፈልጎ እንዲያገኝ የሚችልበትን አቅምም እግዚአብሔር እንዳስታጠቀው ታምናለች፡፡

- ሰዎችም ጥበብን ፈልገው ከሚያገኙባቸው መንገዶች አንደኛው መጽሐፍን ማንበብ ነው፡፡

# ቤተ-ክርስቲያን እና ጥበብ

- ቤተ-ክርስቲያን ከሁሉም በላይ ትኩረት የምታደርገው ግን መንፈሳዊ የሆነው ጥበብ ላይ ነው፡፡

σοφία ⟶ חָכְמָה

# ቤተ—ክርስቲያን እና ንባብ

- በዚህ ምክንያት ቤተ-ክርስቲያን ዘወትር ልጆቿ እንዲያነቡ ትመክራለች፡፡

- በተለይ ደግሞ መንፈሳዊ የሆኑ መጻሕፍትን ከጸሎት ጋር እንዲያነቡ ታበረታታለች፡፡

- ጌታችን ‹አላነበባችሁም?› ብሎ አይሁድን እንደጠየቀ እና አለማወቃቸውን እንደገሰጸ እኛም ላይ እንዲህ እንዳይደርስ መጠንቀቅ ይገባናል፡፡ ይህ እንዳይሆን ቤተክርስቲያን ግጻዌን አዘጋጅታ ሁሌም ለልጆቿ ቅዱስ ቃሉን ታነባለች፡፡

**አእምሯችሁ እና ልባችሁ በመንፈሳዊ መጻሕፍት ንባብ ሲጠመዱ፤ ሁሌም ሙላትን ታገኛላችሁ። የዚህም ምክንያት የመንፈሳዊ መጻሕፍት ንባብ በእግዚአብሔር እምነት ላይ ጠንካራ መሠረትን ስለሚሰጣችሁ ነው።**

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

# 3.

# ጾም እና ትኩረት

# ጾም እና ትኩረት

- በአእምሮው ሕክምና ዓለም ውስጥ እጅግ አሳሳቢ ከሆኑ በሽታዎች አንዱ አልዛይመር (Alzheimer’s Disease) የተሰኘው በሽታ ነው፡፡

- ይህ በሽታ አንጎላችን በጊዜ ሒደት መጠኑ እየቀነሰ ሄዶ፤ የአእምሯችን ሕዋሳት እንዲሞቱ የሚያደርግ ሲሆን - ከጊዜ በኋላም የሰዎችን የማስታወስ፣ የመግባባት እና የማሰብ ችሎታ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ስማቸውን እና ማንነታቸውን የማያስታውሱበትም ደረጃ ያደርሳቸዋል፡፡

- በዚህ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች፤ በ 2050 ዓ.ም በዓለም ዙሪያ የአልዛይመር ተጠቂዎች ቁጥር በእጥፍ እንደሚጨምር ስጋታቸውን አስቀምጠዋል፡፡

# አልዛይመር እና አእምሮ

አንጎላችን በጊዜ ሒደት መጠኑ እየቀነሰ ሄዶ፤ የአእምሯችን ሕዋሳት እንዲሞቱ በማድረግ ለከፍተኛ መርሳት ያጋልጣል፡፡



# ጾም እና ትኩረት

- በዚህ በሽታ ላይ ጥናት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች፤ ይህ በሽታ ለመከላከል ሰውነት የሚያገኘውን ጉልበት በመገደብ ላይ የተመሠረተ መፍትሔ እንደሚያስፈልገው ይናገራሉ፡፡

- ለዚህም መፍትሔ ያሉት ጾምን ነው፡፡

- ጾም የነፍስን ቁስል ከመፈወስ ባለፈ፤ ለአእምሮ እና አካል ጤና የሚጫወተውን አስተዋጽኦ የሚያሳይ ነው፡፡

“

**እኔ የምጸመው ከፍተኛ የሰውነት እና የአእምሮ ቅልጥፍና እንዲኖረኝ ነው።**

ፕሌቶ

“

*ጾም ታላቋ በውስጣችን የምትገኝ መድኃኒት ናት*

ፊሊፐስ ፓራሴልሰስ

# ጾም እና ትኩረት

- ለአልዛይመር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ከመጠን ያለፈ ውፍረት (Obesity) ነው፡፡

- በመሆኑም የሚጾም ሰው አንድም ካለመጠን የሚመጣ ውፍረትን፤ አንድም ደግሞ በአልዛይመር ምክንያት ከሚመጣ ከፍተኛ የመርሳት በሽታ ራሱን ያድናል፡፡

- የጥንት አባቶቻችን ጾምን የሰማዕታት ማሰልጠኛ ይሉት ነበር፡፡ በምግብ ራስን መግዛትን እና ሰውነቱን መቆጣጠርን ያልለመደ ሰው፤ ሰማዕትነት በመጣ ጊዜ ራሱን ለክርስቶስ ሊሰጥ አይቻለውምና፡፡



# ሜታቦሊዝም

ጾም ሰውነታችን ምግብ የሚፈጭበት አጠቃላይ ሒደት ላይ ተጽእኖ አለው፡፡ አእምሯችንም ለዚህ ሒደት ውስጥ Adaptive Brain Response በመግባት ሥራውን ያቀላጥፋል፡፡

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር!